

**SPECIAL EDUCATION RESOURCE HUB:**
**What Families & Students Need to Know this Year**

# I THINK MY CHILD MAY HAVE A DISABILITY

PAGE


**2** ለእርዳታ ማንን ማግኘት እንደሚገባ

1. እኔ እድሜው ከ3 በታች የሆነ ልጄ እድገት በተመለከተ ስጋቶች አሉኝ፣ ለእርዳታ ማንን ማግኘት እችላለሁ?
2. እኔ እድሜው ከ3-5 የሆነው ልጄ እድገት በተመለከተ ስጋቶች አሉኝ። እኔ ለእርዳታ ማንን ማግኘት እችላለሁ?
3. ልጄ በትምህርት ቤት ውስጥ እየታገለ ነው። ልጄ ልዩ የትምህርት ግብዓቶች እንደሚያስፈልገው እንዴት ማወቅ እችላለሁ?

**3** ለልዩ ትምህርት አዲስ

4. ልጄ የአካል ጉደለት እንዳለበት አሁን በምርምራ ተረጋግጧል። ይህ ምን ማለት እንደሆነ እንድረዳ የሚያስችለኝ ምን ግብዓቶች አሉ?

**3** የልጅዎ መብቶች

5. ልጄ የአካል ጉድለት እንዳለበት በምርመራ ተረጋግጧል። ከነሱ ትምህርት ቤት ምን አይነት ድጋፎችን እጠብቃለሁ?

**4** በዚህ የትምህርት አመት ምን መጠበቅ እንደሚገባ

6. COVID-19 ባለበት ሁኔታ፣ በመጪው አመት ከልጄ ትምህርት ቤት ምን አይነት ድጋፍ እጠብቃለሁ?

**4** በዚህ አመት ልጅዎን እና ቤተሰብዎን መደገፍ

7. ልጄ ቤት ውስጥ የሚያስፈልገውን ድጋፍ እያገኘ መሆኑን ለማረጋገጥ ትምህርት ቤቴን መጠየቅ ያለብኝ ጥያቄዎች ምንድን ናቸው?
8. በትምህርት ቤት ውስጥ እኔ እና ልጄ ልናገኝ የሚገባን አገልግሎቶች እና ድጋፎችን አስመልክቶ እንዴት መከራከር እችላለሁ?
9. እኔ እና ልጄ ከትምህርት ቤቴ የሚያስፈልገንን ድጋፍ ካላገኘን የት መሄድ እችላለሁ?
10. በዚህ የርቀት ትምህርት ወቅት ልጄን በተሻለ ሁኔታ ቤት ውስጥ እንዴት ልደግፈው እችላለሁ?
11. በዚህ ወቅት ጭንቀትን ለመቋቋም እና ለደህንነት ቤተሰቤ ምን ማድረግ ይችላል?



# SPECIAL EDUCATION RESOURCE HUB:
## What Families & Students Need to Know this Year

# I THINK MY CHILD MAY HAVE A DISABILITY

## ለእርዳታ ማንን ማግኘት እንደሚገባ

### 1 እኔ እድሜው ከ3 በታች የሆነ ልጄ እድገት በተመለከተ ስጋቶች አሉኝ፣ ለእርዳታ ማንን ማግኘት እችላለሁ?

እርስዎ፣ ቤተሰብዎ ወይም የልጅዎ ሀኪም ልጅዎ ከሌሎች ልጆች የተለየ እድገት እንዳለው ሊያስተውሉ ይችላሉ። ይህ ሊያስጨንቅ ይችላል፣ ነገር ግን ሊረዳዎ የሚችሉ ግብዓቶች አሉ።

ስጋቶች ካሎት፣ Strong Start፣ የDC የቀደመ የጣልቃገብነት ፕሮግራምም ያግኙ፣ በመደወል በ (202) 727-3665። Strong Start በOSSE አማካኝነት የሚተዳደር ነው እና የአካል ጉድለት ወይም የእድገት መዘግየቶች ላለባቸው ጨቅላ ህጻናት እና ታዳጊ ልጆች እና ቤተሰቦቻቸው ነጻ ድጋፍ እና አገልግሎቶች ይሰጣል። የእነሱ ቡድን መብቶቻቹን ይገልጹላቸዋል፣ ልጅዎ ለቀደመ የጣልቃገብ አገልግሎቶች ብቁ መሆኑን ይወስናሉ፣ እና የልጅዎን ፍላጎቶች እና የእለት ተለት የእንቅስቃሴ ሁኔታዎች የልጅዎን ትምህርት ለማሳደግ እንዲጠቀሙባቸው የእርስዎን የራስ መተማመን ለመገንባት ያግዛል። ይህ የStrong Start Road Map በሂደቱ ላይ ያሉትን እያንዳንዱን እርምጃዎች ይገልጻል።

ሊገኙ የሚችሉ አገልግሎቶች ጥቂት ምሳሌዎች የሚከተሉት ናቸው፣

- የእድገት ምርመራዎች
- ንግግር፣ አካላዊ፣ ኦኩፔሽናል እና የእድገት ቴራፒዎች (ህክምናዎች)
- የመስማት ወይም የእይታ አገልግሎቶች
- የአገልግሎቶች ቅንጅት

ስለህጻናት ልጆች የበለጠ መረጃ፣ የሚከተሉትን ግብዓቶች ማየት ይችላሉ።

- Strong Start ብሮሸር
- የCDC የእድገት ምእራፎች
- ቤተሰቦች መብቶች አሏቸው፣ IDEA ክፍል ሐ ስነስርአታዊ ጥንቃቄዎች

### 2 እኔ እድሜው ከ3-5 የሆነው ልጄ እድገት በተመለከተ ስጋቶች አሉኝ። እኔ ለእርዳታ ማንን ማግኘት እችላለሁ?

እድሜው 3-5 የሆነ ልጅዎ ስጋቶች ካሎት፣እርስዎን ለመርዳት DCPS Early Stages እዚህ ይገኛል። DC የህዝብ ትምህርት Early Stages፣ እድሜያቸው 2 አመት፣ ከ8 ወር እስከ 5 አመት፣ 10 ወር ያሉ ልጆች የግምገማ ማእከል ነው። እነሱ ልጅዎ ሊኖረው የሚችል ማንኛውንም መዘግየቶች ለመለየት ይረዳሉ፣ እና በእርስዎ ፍቃደኝነት እና ተሳትፎ እነሱን ለመፍታት የሚያስችሉ አገልግሎቶችን ያመቻቻሉ። አገልግሎታቸው ነጻ እና በDC ውስጥ ለሚኖሩ ወይም ለሚማሩ ሁሉም ተማሪዎች ክፍት ናቸው።

ልጅዎ የDC የህዝብ ቻርተር ትምህርት ቤት እየተማረ ከሆነ፣ለምርመራ በትምህርት ቤቱ ውስጥ ያለ ማንኛውንም ሰው መጠየቅ ይችላሉ።

ከተቻለ ፣እባክዎ ምርመራ እንዲደረግ የሚቀርቡ ጥያቄዎችን በጽሁፍ (ኢሜይል ወይም ደብዳቤ) ያድርጓቸው። ነገር ግን DC Early Stages ወይም ልጅዎ የተመዘገበበት ትምህርት ቤት የቃል የምርመራ ጥያቄዎችን እንዲቀበል ያስፈልጋል።

### 3 ልጄ በትምህርት ቤት ውስጥ እየታገለ ነው። ልጄ ልዩ የትምህርት ግብዓቶች እንደሚያስፈልገው እንዴት ማወቅ እችላለሁ?

ልጅዎ በትምህርት ቤት ሲታገል ማየት ሊያስጨንቅ ይችላል። ልጅዎ የአካል ጉድለት ሊኖርበት እንደሚችል ካሰቡ፣ ልዩ የትምህርት አገልግሎቶች ሊረዳው እንደሚችል ማወቅ የሚቻልበት ሂደት አለ። ይህን ሂደት ከልጅዎ ጋር በማውራት ሊጀምሩ ይችላሉ። ስጋቶችዎን ይግለጹ እና ለልጅዎ “ምርመራ” እንዲደረግ ይጠይቁ። ጥያቄዎ ሂደቱን እንደሚከተለው ያስጀምረዋል፣

1) ሪፈራል፣ ትምህርት ቤቱ የልጅዎን ሁሉንም መረጃ በመገምገም ይጀምራል። ይህ ግምገማ የሚደረገው የሚገኘው መረጃ ልጅዎ የአካል ጉድለት እንዳለበት እንዲጠራጠሩ ሊያደርጋቸው የሚችል መሆኑን ለመለየት ነው።
   - እነሱ ልጅዎ የአካል ጉድለት እንዳለበት ከጠረጠሩ፣ ለምርመራ የእርስዎን ፍቃድ ይጠይቃሉ። ይህ ማለት ከታች ወዳለው ቀጣዩ እርምጃ ይሸጋገራሉ ማለት ነው።
   - መረጃው ሊኖር ስለሚችል የአካል ጉድለት ስጋቶችን የማያስነሳ መሆኑን ከወሰኑ፣ ያንን አስመልክቶ የጹሁፍ ማስታወቂያ ለእርስዎ ይልካሉ። ይህ ማለት ልጅዎ አይመረመርም ማለት ነው። እነሱ ልጅዎ ላለመመርመር ከወሰኑ እና እርስዎ ካልተስማሙ፣ ይህን ውሳኔ ለመሟገት አማራጮች አሎት።
2) ምርመራ፣ ልጅዎ ለልዩ ትምህርት ብቁ የሚያደርግ የአካል ጉድለት ካለበት ትምህርት ቤትዎ አንድ ቡድን ያሰባስባል። ይህ ቡድን ስለ ልጅዎ ያላቸውን መረጃ የሚገመግምና ግምገማውን ለማጠናቀቅ አዲስ መረጃዎችን መሰብሰብ ሊኖርበት ይችላል። ለልጅዎ ትምህርት ወይም ሥነ ልቦናዊ ምዘና በመስጠት አዲስ መረጃ ሊሰበስቡ ይችላሉ።
3) ብቃት፣ ስለ ምርመራው ለመነጋገር የባለሙያ ቡድን ከእርስዎ ጋር ይገናኛል። ልጅዎ ለልዩ ትምህርት አገልግሎቶች “ብቁ” መሆኑን ወይም አለመሆኑን ከእርስዎ ጋር ይወያያሉ። የብቃት ማረጋገጫ በልዩ ትምህርት ህጉ ላይ የተመሠረተ ነው። የፌደራል ህጉ የልዩ ትምህርት ግላዊ የአካል ጉድለት ያለባቸው ግለሰቦች የትምህርት ህግ (Individuals with Disabilities Education Act, IDEA) ተብሎ ይጠራል።

4) ግላዊ የትምህርት ፕሮግራም (Individualized Education Program, IEP) ይዘጋጃል፣ ልጅዎ ለልዩ ትምህርት ብቁ ከሆኑ፣ ለልጅዎ IEP ይዘጋጃል። IEP የልጅዎን ግቦች፣ጥንካሬዎች እና ልዩ ፍላጎቶችን የሚያካትት የጽሁፍ ሰነድ ነው። ልጅዎ እነዚህን ግቦች ላይ ለመድረስ እንዲችል ትምህርት ቤትዎ የሚሰጠውን አገልግሎት እና ድጋፍ ይገልጻል። ይህ ሰነድ በልጅዎ IEP ቡድን ይዘጋጃል። እንደ ወላጅነትዎ፣ እርስዎ የዚህ ቡድን እኩል አባል ኖት። የልጅዎ የልዩ ትምህርት ማግኘት ወይም አለማግኘት የእርስዎ ምርጫ ነው።

ልጅዎ የልዩ ትምህርት አገልግሎቶች የማይፈልግ ቢሆንም፣ በሌሎች ድጋፎች ተጠቃሚ ሊሆን ይችላል። እነዚህ ሌሎች ድጋፎች የ“504 plan” አካል ሊሆኑ ይችላሉ። ለበለጠ መረጃ፣ የልጅዎን ትምህርት ቤት ማነጋገር ይችላሉ ወይም በOSSE’s Section 504 ድረገጽ የበለጠ ማንበብ ይችላሉ።

በሂደቱ ላይ የእነዚህ እርምጃዎች የጊዜ ሰሌዳ በCOVID-19 ምክንያት ሊዘገይ ይችላል። ለምሳሌ፣ በአካል መገናኘት አለመቻል ምርመራዉን ለማድረግ አስቸጋሪ ሊያደርገው ይችላል። በሚቻልበት ጊዜ ትምህርት ቤቱ ምርመራዎችን ለማድረግ ፈጠራ የታከለበት እና ተለዋዋጭ አማራጮችን ለማቅረብ ከእርስዎ ጋር ሊሰሩ ይገባል። ወደ ፊት መጓዝ ካልተቻለ፣ ከትምህርት ቤቱ ይህን የሚገልጽ የጽሁፍ ማስታወቂያ ሊደርስዎ ይገባል። በተጨማሪ አዲስ የመጨረሻ የጊዜ ገደብ ላይ ለመስማማት ከትምህርት ቤትዎ ጋር ሊሰሩ ይችላሉ።

እነዚህ ግብዓቶች የበለጠ መረጃ አላቸው፣

- OSSE የልዩ ትምህርት የወላጅ ብሮሸር
- Understood.org - 6 ልጅዎ እንዲመረመር የማድረግ ጥቅሞች
- የተማሪ ተሟጋች ቢሮ- የወላጅ እና የቤተሰብ-መምሪያ

## ለልዩ ትምህርት አዲስ

**4** ልጄ የአካል ጉደለት እንዳለበት አሁን በምርምራ ተረጋግጧል። ይህ ምን ማለት እንደሆነ እንድረዳ የሚያስችለኝ ምን ግብዓቶች አሉ?

የበለጠ እንዲማሩ እና ልጅዎን ለመደገፍ የሚረዳዎ ብዙ ግብዓቶች አሉ። የሚከተሉት ሊጠቅሙ የሚችሉ የተወሰኑ ነገሮች ናቸው፣

ማየት የሚችሏቸው ግብዓቶች፣

- ስለልዩ የትምህርት አገልግሎቶች በወላጆች አዘውትረው የሚጠየቁ ጥያቄዎች
- Understood.org ስለአንድ የተለየ የአካል ጉድለት አይነት የበለጠ መማር የሚችሉት እና ከሌሎች ቤተሰቦች ጋር የሚገናኙበት ግብአት ነው። በድረገጻቸው ላይ ያሉ የተወሰኑ ጠቃሚ ሊንኮች(አገናኝ መስመሮች) የሚከተሉት ናቸው፣
    - ልዩ ትምህርትን መረዳት
    - በIDEA ስር 13 የአካል ጉድለት ምድቦች
    - IEP ዎችን መረዳት
    - የቃላት እና የትርጉሞች ዝርዝር

ማናገር የሚችሏቸው ሰዎች፣

- የፍትህ እና የትምህርት ተሟጋቾች (Advocates for Justice and Education, AJE) የDC የአካል ጉድለት ያለባቸው ተማሪዎች ቤተሰቦች የስልጠና እና የመረጃ ማእከል ነው።
- የDC የመንግስት የልዩ ትምህርት አማካሪ ፓነል (State Advisory Panel on Special Education, SAPSE) ለህዝብ ክፍት ናቸው እና ከሌሎች ቤተሰቦች ጋር ለመገናኘት ትልቅ መንገድ ነው።

## የልጅዎ መብቶች

**5** ልጄ የአካል ጉድለት እንዳለበት በምርመራ ተረጋግጧል። ከነሱ ትምህርት ቤት ምን አይነት ድጋፎችን እጠብቃለሁ?

ትምህርት ቤትዎ የልጅዎን ልዩ ፍላጎቶች ሊያሟላ የሚችል በልዩ ሁኔታ የታቀደ ትምህርት ያለምንም ወጪ ለልጅዎ ይሰጣል። ይህ የሚከተለውን ያካትታል፣

- ልጅዎ በልዩ ሁኔታ የታቀደ ትምህርት ያገኛሉ። ፍላጎቶቻቸውን መሰረት በማድረግ፣ እነሱ በተጨማሪ ለንግግር ቴራፒ (ህክምና) ወይም የካውንስሊንግ አገልግሎቶችን ለማግኘት ብቁ ሊሆኑ ይችላሉ።
- ወላጅ የሆኑትን እርስዎን ጨምሮ አስተማሪዎችን እና ሌሎችን የያዘ ቡድን፣ ተማሪው የሚያገኘውን አገልግሎቶች እና ድጋፍ ይወስናል።
- ይህን ትምህርት የመስጠት እቅድ በግላዊ የትምህርት ፕሮግራም (IEP) መጻፍ አለበት።
- ትምህርት ቤትዎ በመላው የትምህርት አመት ሪፖርቶች ወይም ማሻሻያዎችን ይሰጠዎታል። በተጨማሪ ያሎትን ማናቸውም ስጋቶች መወያየት ይችላሉ።
- እርስዎ እንደወላጅነትዎ የልጅዎን ልዩ ፍላጎቶች ለመረዳት እና ለማገዝ እንዲረዳዎ የልጅዎ የIEP አካል የሆነ ስልጠና ሊያገኙ ይችላሉ።

የፌደራል ህግ የሆነው፣የአካል ጉድለት ያለባቸው ሰዎች የትምህርት ህግ (IDEA) “ነጻ እና ተገቢ የሆነ የህዝብ ትምህርት ” (FAPE በመባል በተጨማሪ የሚታወቀውን) መብትን፣የአካል ጉድለት ላለባቸው ልጆች ይጠብቃል። ይህ መብት ልጅዎ በ DCPS ትምህርት ቤት ወይም የDC የህዝብ ቻርተር ትምህርት ቤት የተመዘገበ ቢሆንም፣ ወይም የህዝብ ያልሆነ የልዩ ትምህርት ትምህርት ቤት ውስጥ የሚማር ቢሆንም ተፈጻሚ ነው።.

በተጨማሪ IDEA፣ ልጅዎ FAPE ማግኘቱን ለማረጋገጥ “ስነስርዓታዊ ጥበቃዎች” ተብለው የሚታወቁ ሌሎች ብዙ መብቶችን ይጠብቃል። የOSSE ስነስርዓታዊ ጥበቃዎች ማስታወቂያ የእነዚህ መብቶች የበለጠ ዝርዝር ገለጻዎች አለው።

COVID-19 የልጅዎን መብቶች አይቀይርም። ልጅዎ ትምህርት ቤት ውስጥ ወይም ቨርቹዋል የሚማር ቢሆንም እነዚህ ተመሳሳይ ናቸው። ነገር ግን በዚህ አመት፣ ልዩ ትምህርት ለልጅዎ የተለየ አይነት እና የተለየ ስሜት ሊኖረው ይችላል። “በቀጣዩ አመት፣COVID-19 ባለበት ሁኔታ ከልጄ ትምህርት ቤት ምን አይነት ድጋፍ እጠብቃለሁ?”፣ የሚለው ጥያቄ ስለዚህ የበለጠ መረጃ ይሰጣል።

ጥያቄዎች ካሎት፣ የልጅዎን አስተማሪ ወይም የልዩ ትምህርት አስተባባሪውን ያነጋግሩ

## በዚህ የትምህርት አመት ምን መጠበቅ እንደሚገባ

**6** COVID-19 ባለበት ሁኔታ፣ በመጪው አመት ከልጄ ትምህርት ቤት ምን አይነት ድጋፍ እጠብቃለሁ?

ትምህርት ቤትዎ ለዚህ የትምህርት አመት እቅድ ላይ ጠንክሮ ሰርቷል። ከታች ያሉት እርስዎ እና ልጅዎ ከትምህርት ቤትዎ የሚጠብቋቸው ቁልፍ ነገሮችን ያካትታሉ። ጥያቄዎች ካሉት፣ ትምህርት ቤትዎን ያግኙ።

1) ምንም እንኳን በአካል ትምህርት ባይኖርም፣ የርስዎ ትምህርት ቤት ልዩ ትምህርትን መስጠት መቀጠል አለባቸው። ይህ የቤተሰብዎን የጤና እና የደህንነት ፍላጎቶችን በማጣጣም በርቀት የትምህርት ሞዴል ሊሰጥ የሚችለውን፣በልጅዎ ግላዊ የትምህርት ፕሮግራም የሚጠየቀውን ልዩ ትምህርትን ማግኘት ያካትታል። ነገር ግን፣ በርቀት ትምህርት ወቅት የተወሰኑ ትምህርቶች እና አገልግሎቶች የተለዩ ሊመስሉ ይችላሉ። ለምሳሌ፣
   - የልጅዎን የአካል ጉድለት [ለማጣጣም መማር የተወሰኑ ቨርቹዋል መንገዶችን ሊያካትት ይችላል።](#)
   - የአገልግሎት አቅራቢዎችን በስልክ ወይም በቪዲዮ ሊያገኟቸው ይችላሉ።
   - ልጅዎ በቤት ውስጥ ስራ ለመስራት የሚያግዝ አዲስ ቴክኖሎጂ ሊያስፈልጋቸው ይችላል (“ደጋፊ ቴክኖሎጂ” ተብሎ ይጠራል)። ይህ ለርቀት ትምህርት አገልግሎት ላይ ከሚውለው መሳርያ የተለየ ነው እና ጽሁፍን የሚያስተልቅ ወይም ጮክ ብሎ ለማንበብ የሚያስችል ሶፍትዌርን ሊያካትት ይችላል።

   ከልጅዎ ትምህርት ቤት ጋር መሰጠት ያልቻሉ አገልግሎቶችን በዚህ አመት እንዴት ማካካስ እንደሚቻል መወያየት ይችላሉ።

2) የእርስዎ ትምህርት ቤት፣ የልጅዎን IEP ለመመርመር እና ለማሻሻል እንደአስፈላጊነቱ ከእርስዎ ጋር አጋር መሆን አለባቸው። ለልጅዎ አስፈላጊ ከሆነ፣ ይህ ሂደት የልጅዎ ፍላጎቶች በምን መልኩ እንደተቀየሩ እና ልጅዎ በቤት ውስጥ ወይም ትምህርት ቤት ቢማሩ እንዲዚህ ፍላጎቶች እንዴት ሊሟሉ እንደሚችሉ ማየት አለበት። በተጨማሪ ልጅዎን ለመደገፍ እርስዎ እንደወላጅነትዎ የሚያስፈልግዎትን ስልጠና ማየት አለበት። ልጅዎ የDCPS ትምህርት ቤት ውስጥ የሚማሩ ከሆነ፣ [DCPS ለእያንዳንዱ የአካል ጉድለት ላለበት ተማሪ የርቀት ትምህርት እቅድ በማዘጋጀት ታትሯል።](#)

3) የእርስዎ ትምህርት ቤት የልጅዎን የትምህርት ደረጃ በትምህርት አመቱ መጀመርያ ላይ መፈተን እና እነዚያን ውጤቶች ለእርስዎ ማጋራት አለበት። ይህ ፈተና፣ “መረጃ ሰጭ ምዘና” ተብሎ የሚታወቀው፣ የልጅዎ ፍላጎቶች እንዴት እንደተቀየረ ትምህርት ቤቱ እንዲረዳ ይረዳዋል።

4) ትምህርት ቤትዎ ልጅዎን እንዲረዱ ሊረዳዎ ይገባል። ይህ ለርቀት ትምህርት ስልጠናን እና ግብዓቶችን ማቅረብን ያካትታል። እነሱ በተጨማሪ አዲስ ቴክኖሎጂን እንዴት መጠቀም እንደሚቻል እርስዎን ማስተማር አለባቸው።

5) ትምህርት ቤትዎ በትምህርት ቤት የመጀመሪያዎቹ ሁለት ሳምንቶች ላይ እነዚህን እርምጃዎች እንዴት እንደሚወስዱ ለእርስዎ መግለጽ አለባቸው። ትምህርት ቤትዎ “ቀጣይነት ያለው ትምህርት እና የትምህርት ቤት የማገገሚያ እቅድ” የሚል እቅድ እያዘጋጀ ነበር። ይህ እቅድ ከእርስዎ ጋር በቀጥታ ይጋራል። በተጨማሪ አንዴ ከተጠናቀቀ በኋላ፣የትምህርት ቤትዎ የኔትዎርክ ድረገጽ ላይ እና [በOSSE ድረገጽ](#) ውስጥ ይኖራል። ይህ እቅድ ሌሎች ነገሮችን ጨምሮ፣ ትምህርት ቤትዎ የሚከተሉትን እንዴት እንደሚያደርግ ያብራራል፣
   - ተማሪዎችን ቤት ውስጥ እና በአካል ማስተማር
   - በትምህርት ገበታ ላይ መገኘትን መከታተል
   - ቤተሰቦችን ከሚያስፈልገው ቴክኖሎጂ ጋር ማገናኘት
   - ለርቀት ትምህርት የአካዳሚክ፣ የባህርይ እና ልዩ ድጋፎችን እንደሚያካትት

ስለእነዚህ ግቦች የበለጠ ያንብቡ በ [OSSE ቀጣይነት ያለው የትምህርት መርህዎች](#) እና [የOSSE IDEA፣የFAPE አንቀጽ ክፍል B፣ የርቀት እና የድብልቅ ትምህርቶች ጋር የተያያዘ መመሪያ።](#)

እዚህ የትምህርት ቤት የመገኛ መረጃ ሊያገኙ ይችላሉ፣

- [DC የህዝብ ትምህርት](#)
- [DC የህዝብ ቻርተር ትምህርት ቤቶች](#)
- [የህዝብ ያልሆነ የልዩ ትምህርት ትምህርት ቤቶች](#)

## በዚህ አመት ልጅዎን እና ቤተሰብዎን መደገፍ

**7** ልጄ ቤት ውስጥ የሚያስፈልገውን ድጋፍ እያገኘ መሆኑን ለማረጋገጥ ትምህርት ቤቴን መጠየቅ ያለብኝ ጥያቄዎች ምንድን ናቸው?

የእርስዎ ትምህርት ቤት ለዚህ አዲስ የትምህርት አመት የአካል ጉድለት ያለባቸውን ተማሪዎች እንዴት መደገፍ እንደሚችል ሲያቅድ ነበር። የእርስዎ ትምህርት ቤት ትምህርት ቤት በተጀመረ በመጀመርያዎቹ ሁለት ሳምንቶች ልጅዎን የሚደግፉበትን እቅድ ማጋራት አለባቸው። እነሱ በተጨማሪ በድረገጻቸው ይህን መረጃ ማስቀመጥ አለባቸው።

የበለጠ ለማወቅ የልጅዎን አስተማሪ ወይም የልዩ ትምህርት አስተባባሪ ሊጠይቋቸው የሚችሉ ጥቂት ጥያቄዎች የሚከተሉትን ይመስላሉ፣

የመላው ትምህርት ቤት የዚህ አመት የትምህርት ቤት እቅዶች፣

- በዚህ ትምህርት ቤት ለሁሉም ተማሪዎች የሚሰጡ ድጋፎች እና አገልግሎቶች ምንድን ናቸው? ለልጄ እና ለቤተሰቤ ተጨማሪ ድጋፎች ይኖራሉ?
- ቴክኖሎጂን እንዴት እየመረጣቹ ነው? ልጄ ሊጠቀመው እንደሚችል በምን መልኩ እያረጋገጣቹ ነው?
- ልጄ ከአስተማሪዎቹ ጋር በየቀኑ ምን ያክል ጊዜ ይኖረዋል?

የመማር ግቦች፣

- በልጄ ግላዊ የትምህርት ፕሮግራም (IEP) ላይ የትኞቹ አገልግሎቶች ኦንላይን ይሆናሉ?
- የልጄ እድገት ቨርቹዋል በሆነ መንገድ እንዴት ይገመገማል? ይህ ምን ሊመስል ይችላል? እኔ ቤት ውስጥ እንዴት መርዳት እችላለሁ?
- የትምህርት ቤቱ የጊዜ ሰሌዳ እና የግምገማ እቅድ ምንድን ነው፣ እና አስፈላጊ ሲሆን፣ የባህርይ ልዩነቶችን አይነት ተማሪ ተኮር በሆነ ምክንያት IEPዎችን የመከለስ እቅዳቸው ምንድን ነው?
- በዚህ ጸደይ ለልጄ ውጤታማ የሆነው እና ያልሆነው ምንድን ነው? ያንን መሰረት በማድረግ ምን አይነት ማስተካከያዎችን ማድረግ እንችላለን?

ለበለጠ ጥያቄዎች ትምህርት ቤትዎን መጠየቅ ይችላሉ፣ እዚህ ይመልከቱ፣

- በCOVID-19 ወቅት የአካል ጉድለቶች ያሉባቸው ተማሪዎች ወላጆች ከፍተኛ ጠቃሚ ምክሮች
- የመማር ጉድለት ላለባቸው ብሄራዊ ማእከል

እዚህ፣ የትምህርት ቤት ፕሮፋይሎችን ከሚገኙበት አድራሻ ጋር ማግኘት ይችላሉ፣

- DC የህዝብ ትምህርት
- DC የህዝብ ቻርተር ትምህርት ቤቶች
- የህዝብ ያልሆነ የልዩ ትምህርት ትምህርት ቤቶች

## 8 በትምህርት ቤት ውስጥ እኔ እና ልጄ ልናገኝ የሚገባን አገልግሎቶች እና ድጋፎችን አስመልክቶ እንዴት መከራከር እችላለሁ?

ልጅዎ የተመዘገበበት የDC ትምህርት ቤት ስለልጅዎ መከራከር የሚጀምሩበት የመጀመርያው ቦታ ነው። ስጋቶች ካሎት፣ ከልጅዎ የDC ትምህርት ቤት ጋር ማጋራት ይጀምሩ። እርስዎ የልጅዎን አስተማሪ፣ የልዩ ትምህርት አስተባባሪ ወይም ሌሎች የትምህርት ቤት ሀላፊዎችን ማግኘት ይችላሉ።

ስለዚህ ጉዳይ በስክል፣ በኢሜይል ወይም በቪድዮ ማውራት ይችላሉ። የሚከተሉት ሊረዱ የሚችሉ የግብዓቶች እና የደብዳቤዎች ናሙና ናቸው።

በDC ውስጥ ያሉ የተለያዩ ድርጅቶች እንዲከራከሩ ይረዳሉ። እነሱ በተጨማሪ ከትምህርት ቤትዎ ጋር ለመስራት ከተቸገሩ ስለሚኖሩት ቀጣይ እርምጃዎች ሊነግርዎ ይችላሉ። እነዚህ ድርጅቶች የሚከተሉት ናቸው፣

- የተማሪ ተሟጋች ቢሮ፣ የDC ተማሪዎችን እና ቤተሰቦችን በወላጅ ትምህርት፣ ማሰልጠን፣ ግብዓቶች እና ስልጠና ይረዳል።
- የእምባ ጠባቂ ቢሮ፣ በDC ውስጥ ስላሉ የህዝብ ትምህርት አስመልክቶ ወላጆች ያላቸውን ስጋቶች ለመርዳት ድርድርን እና ሽምግልናን የሚጠቀም ገለልተኛ ቢሮ።
- የፍትህ እና የትምህርት ተሟጋቾች (AJE)፣ የDC የወላጅ ስልጠና እና የመረጃ ማእከል። እነሱ ወላጆች ልጆቻቸውን ወክለው እንዲከራከሩ እና የወላጅ ስልጠና እና ግብዓቶችን በማቅረብ ይረዳሉ።

## 9 እኔ እና ልጄ ከትምህርት ቤቴ የሚያስፈልገንን ድጋፍ ካላገኘን የት መሄድ እችላለሁ?

ከሞከሩ እና ከትምህርት ቤቱ ጋር ስለልዩ የትምህርት ጉዳዮች ላይ ስምምነት ላይ ካልደረሳቹ፣ እርስዎ ሌሎች አማራጮች አሎት። ልጅዎ የDCPS ትምህርት ቤት ውስጥ የሚማሩ ከሆነ፣ ድጋፍ ለመጠየቅ መጀመርያ የDCPS Office of Integrity ማግኘት ይችላሉ። ካልሆነ፣ የOSSE የግልግል ዳኝነት ቢሮ ወይም የመንግስት የአቤቱታዎች ቢሮ

ለሚከተሉት እርምጃዎች የሚኬድባቸው የመጀመርያ ስፍራዎች ናቸው፣

- የተሳለጠ ግላዊ የትምህርት ፕሮግራም (IEP) ስብሰባ ፣ በገለልተኛ ሰው የሚመራ የIEP ቡድን ስብሰባ። ይህ ሊያስቡበት የሚገባ የመጀመርያው እርምጃ ሊሆን ይችላል። ልጅዎን በደምብ በሚያውቋቸው ሰዎች መካከል ችግሮችን በፍጥነት ለመፍታት እድል ይሰጥዎታል።
- ድርድር፣ በገለልተኛ ሶስተኛ ወገን የሚመራ ውይይት። ግቡ ትምህርት ቤቱ እና እርስዎ ስምምነት ላይ እንድትደርሱ ነው። ይህ በአብዛኛውን ጊዜ ከፍትህዊ ሂደት ይፈጥናል።
- ፍትህዊ የክርክር ሂደት፣ እርስዎ እና ትምህርት ቤቱ ሁለታችሁም የየራሳቹን ክርክር በምስክሮች እና አስፈላጊ ሰነዶች በማቀረብ ለገለልተኛ አቤቱታ ሰሚ ባለሞያ ታቀርባላቹ። አቤቱታ ሰሚው ባለሞያ ውሳኔ ይሰጣል። በዚህ ላይ ይግባኝ ወደ ፍርድ ቤት ማቅረብ ይችላሉ።
- የመንግስት አቤቱታ፣ እርስዎ የጽሁፍ አቤቱታ ለOSSE ያቀርባሉ እና ህጉ መጣሱን ለማረጋገጥ ምርመራ ይደረጋል። የ

ግልግል ዳኝነት ቢሮ የወላጅ መምርያ የበለጠ መረጃ አለው።

## 10 በዚህ የርቀት ትምህርት ወቅት ልጄን በተሻለ ሁኔታ ቤት ውስጥ እንዴት ልደግፈው እችላለሁ?

ለልጅዎ አስተማማኝ እና በፍቅር የተሞላ ቤት በመስጠት እና በትምህርት ላይ እንዲሳተፉ በማድረግ ብዙ ነገር እያደረጉ ነው። በዚህ ጊዜ ልጅዎ ወይም ልጆችዎን ቤት ውስጥ መደገፍ ከአቅም በላይ ሆኖ ሊሰማዎ ይችላል፣ ነገር ግን የልጅዎ አስተማሪዎች ስለእናንተ ያስባሉ እና እርስዎን ለመደገፍ ከጎንዎ ናቸው።

ትምህርት ቤትዎ የልጅዎ የቤት ውስጥ ትምህርት እንዲያግዙ የሚያስችል ስልጠና እና ግብዓቶችን ሊያቀርብ ይገባል። የልጅዎን አስተማሪ ሁሉጊዜ እርዳታ መጠየቅ ይችላሉ።

የሚከተሉት ልጅዎን(ጆችዎን) በቤት ውስጥ ሊያግዟቸው የሚችሉባቸው የተወሰኑ ሀሳቦች ናቸው፣

እነሱ የሚማሩበት ቦታ ያዘጋጁ። ቢቻል፣ ለመማሪያ ብቻ የሚሆን ቦታ ያዘጋጁ። የሀሳብ መበታተንን የሚገድብ እና የተደራጀ ቦታ ለማግኘት ይሞክሩ። ለተጨማሪ ጠቃሚ ምክሮች ቨርቹዋል ትምህርት ቤት የሚለውን ይመልከቱ።

ቀና ቸውን ስርዓት እንዲያስይዙ ያግዟቸው። የርቀት ትምህርት በትምህርት ቤት ውስጥ ካለው ያነሰ ስርዓት አለው። ልጅዎ የጊዜ ሰሌዳ በማዘጋጀት እና አንድ ተግባር ላይ ለመቆየት እርዳታ ሊያስፈልጋቸው ይችላል። ቢቻል፣ ትምህርት ቤት ውስጥ ሊኖር ይችል እንደነበረው አይነት እለታዊ የጊዜ ሰሌዳ ይፍጠሩ።

- የሚከተሉት ፖስተሮች፣ ህትመቶች እና ሌሎች ግብዓቶች ስርዓት ለመገንባት የሚያግዙ ናቸው።

የቴሌቴራፒ እርዳታ። የቴሌቲራፒ ማለት በቨርቹዋል (ምናባዊ) የሚሰጥ ህክምና ማለት ነው። ልጅዎ ውጭ ካሉ ቴራፒስት ወይም ካውንስለር ጋር ቤት ውስጥ እየሰሩ ሊሆን ይችላል። ለቴሌቴራፒ የቤተሰብ ጠቃሚ ምክሮች አስፈላጊ ሲሆን የቪዲዮ ወይም የስልክ ጥሪዎችን ለማድረግ ዝግጁ መሆንን እና የልጅዎ ፊት ለአልግሎት አቅራቢ የሚታይ መሆኑን ማረጋገጥን ያካትታል።

እራስዎን በሚገባ መንከባከብ። የራስዎን የአእምሮ ጤና መጠበቅ አስፈላጊ ነው። የAccess HelpLine ጋር በ1(888) 7WEHELP ወይም 1(888) 793-4357 በመደወል ማግኘት ይችላሉ።

ተጨማሪ ግብዓቶች፣

- ለቤት ውስጥ ትምህርት የቤተሰብ መምሪያ
- የአካል ጉድለት ላለባቸው ተማሪዎች የርቀት ትምህርት ግብዓቶች
- ተመራጭ የልዩ ትምህርት መተግበሪያዎች እና ድረገጾች
- ከባድ ወይም በርካታ የአካል ጉድለቶች ላሉባቸው ተማሪዎች የርቀት ትምህርት
- ልዩ ፍላጎት ያሏቸው ተማሪዎችን ከርቀት ትምህርት ጋር እንዲለማመዱ ማገዝ

## 11 በዚህ ወቅት ጭንቀትን ለመቋቋም እና ለደህንነት ቤተሰቤ ምን ማድረግ ይችላል?

ይህ በመላው DC ለሚገኙ ቤተሰቦች እና ተማሪዎች አስጨናቂ ጊዜ እንደሆነ እናውቃለን። የሚያግዙ በርካታ ግብዓቶች አሉ።

ቨርቹዋል ስልጠና/ዎርክሾፕ ላይ መሳተፍ፣

- DCPS Parent University Online በDC ላሉ ሁሉም ቤተሰቦች የቨርቹዋል ዎርክሾፖች አለው። የወርክሾፕ የጊዜ ሰሌዳ እና ያለፉ ሪከርዶች ኦንላይን ይገኛሉ።
- እርስዎ እድሜው ከ6 አመት በታች የሆነ ልጅ የሚንከባከቡ ከሆነ፣ በአወንታዊ የአስተዳደግ ፕሮግራም ላይ ኦንላይን መሳተፍ ይችላሉ። ይህ ፕሮግራም በDC የባህርይ ጤና ዲፓርትመንት የሚቀርብ ነው። ይህ ፕሮግራም ፈታኝ የሆኑ ሁኔታዎችን መቋቋም እንዲለማመዱ ይረዳዎታል። ፕሮግራሙን ለማግኘት፣ አካውንት ሲፈጥሩ "dcparents"እንደ መግቢያ ቁልፍ ያስገቡ።

የድጋፍ ወይም ግብአቶች መኖር፣

- ከባህርይ ጤና ዲፓርትመንት ግብዓቶች፣
  - የDC Access HelpLine ጋር መደወል ይችላሉ በ1(888) 7WE-HELP ወይም 1(888)793-4357።
  - ይህ ባለ አንድ ገጽ የባህርይ ጤና በራሪ ጽሁፍ ያሉትን የድጋፍ አይነቶች ያብራራል።
  - የባህርይ ጤና ዲፓርትመንት የበለጠ መረጃ እና ግብዓቶች አሉት።
- የበሽታ መቆጣጠር እና መከላከል ማእከላት(CDC) ተማሪዎችን እና ቤተሰቦችን የሚያግዝ የግብዓት ገጽ አለው።
- ለልጅዎ ተጨማሪ ድጋፍ ማግኘት ይፈልጋሉ? ከ"ባህርይ ጤና አስተባባሪ" ጋር ለመገናኘት ትምህርት ቤትዎ ጋር ይደውሉ እና ይጠይቁ። እነሱ ተማሪዎን ከአገልግሎቶች ጋር በማገናኘት ያግዛሉ።

ከሌሎች ቤተሰቦች ጋር ይገናኙ፣

- የመንግስት የልዩ ትምህርት የአማካሪ ፓነል (State Advisory Panel on Special Education, SAPSE) ሌሎች ቤተሰቦችን ሊያገኙበት የሚችሉ ስብሰባዎች አሏቸው።
- በDC የባህርይ ጤና ላይ የቤተሰብ እና የወጣቶች ተሳትፎ ኮሚቴ ቤተሰቦች ልምዶቻቸውን፣ ስጋታቸውን፣ እና ሀሳባቸውን የሚያጋሩበት ስፍራ ነው። ይህ ኮሚቴ በየወሩ ሶስተኛው አርብ ይገናኛል። ኢሜይል ማድረግ ይችላሉ ለዶ/ር Chioma Oruh (ቺዮማ ኦሩህ) በ chioma@drchibornfree.com የቨርቹዋል የስብሰባ ሊንኩን ለማግኘት።
- የUnderstood.org የታሪክ ስብስብ የአካል ጉድለት ያለባቸው ተማሪዎች ቤተሰቦች COVID-19 እንዴት እየተቋቋሙ መሆኑን ያጋራል።